መልእክት ሁለት

**የሐና አገልግሎት**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ 1 ሳሙ. 1፡1—2፡11፤ 18-21፤ 26

I. **የጌታ ምለሳ ምን እንደሆነ መገንዘብ አለብን፤ የጌታ ምለሳ ቅድስቲቱን ከተማ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ለማጠናቀቅ እንደ የክርስቶስ አካል እውነታ ድል ነሺዎቹን በምሳሌ የምታሳየውን ጽዮንን መገንባት ነው፦**

ሀ. ጽዮን የንጉሥ ዳዊት ከተማ (2 ሳሙ. 5፡7)፣ በምድር ላይ እንዳለ የእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ መቅደሱ የተገነባበት የኢየሩሳሌም ከተማ ማዕከል ነበረች (መዝ. 48፡2፤ 9፡11፤ 74፡2፤ 76፡2፤ 135፡21፤ ኢሳ. 8፡18)።

ለ. በብሉይ ኪዳን፣ ጽዮን እንደ ማዕከሏ ያላት የኢየሩሳሌም ከተማ ነበረች፤ በምሳሌ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት የዛሬዋ ኢየሩሳሌም ነው፤ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ፍጹማን የተደረጉና የበሰሉ አምላክ-ሰዎች የሆኑ የድል ነሺዎች ቡድን መኖር አለበት፣ እነዚህም ድል ነሺዎች የዛሬዋ ጽዮን ናቸው—ተዛ. ራእ. 14፡1-5።

ሐ. እንደ ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ድምቀት እና ውበት (መዝ. 48፡2፤ 50፡2)፣ ጽዮን እንደ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ጫፍ፣ ማዕከል፣ ከፍ መደረግ፣ መጠንከር፣ መበልጠግ፣ ውበት፣ እና እውነታ ድል ነሺዎቹን በምሳሌ ታሳያለች (መዝ. 48፡2፤ 11-12፤ 20፡2፤ 53፡6፤ 87፡2)።

መ. የኢየሩሳሌም መለያ ባህሪያት፣ ሕይወት፣ በረከት፣ እና መመሥረት ከጽዮን ይመጣሉ—1 ነገ. 8፡1፤ መዝ. 51፡18፤ 102፡21፤ 128፡5፤ 135፡21፤ ኢሳ. 41፡27፤ ኢዮኤል 3፡17።

ሠ. ድል ነሺዎቹ እንደ ጽዮን የክርስቶስ አካል እውነታ ናቸው እንዲሁም የተጠናቀቀችውን ቅድስቲቱን ከተማ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን፣ ለዘላለም እንደ እግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ ከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ የሆነችውን ቅድስተ ቅዱሳን ለማምጣት በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የአካሉን መገንባት ያጠናቅቃሉ (ራእ. 21፡16፤ ተዛ. ዘጸ. 26፡2-8፤ 1 ነገ. 6፡20)፤ በአዲሱ ሰማይ እና በአዲሱ ምድር መላዋ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ድል ነሺ ከሚሆኑት ከአማኞች ሁሉ ጋር ጽዮን ትሆናለች (ራእ. 21፡1-3፣ 7፣ 16፣ 22)።

ረ. በራእይ መጽሐፍ ጌታ የሚፈልገው እና ጌታ የሚገነባው ጽዮንን፣ ድል ነሺዎቹን ነው፤ በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ውስጥ ያለው የመንፈሳዊው መገለጥ ውስጠ-መሠረታዊ እውነታ ይህ ነው፤ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳደረገው በምንም ዋጋ ለመጸለይ እና ዋጋውን ለመክፈል በእርግጥ ከፍተኛ ፍላጎት ያለን መሆን ያስፈልገናል—ኤፌ. 6፡17-18፤ ቆላ. 4፡2፤ ፊልጵ. 3፡8-14።

ሰ. ጌታ በዚህ ዘመን ላለው የድል ነሺዎች ጥሪ ምላሻችን ሕያው-ንቁ መሆናችን ነው፤ ሕያው-ንቁ መሆን ማለት ከሕያዉ እና ከሚሠራው አምላካችን ጋር በአንድነት ሕያው እና ንቁ መሆን ነው፤ ለዘላለማዊ ኢኮኖሚው መፈጸም የሆነው በምድር ላይ ያለው የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ በሆነ መልኩ በድል ነሺዎቹ በኩል ነው።

ሸ. በዚህች ያለአግባብ በተያዘች ምድር ላይ ሙሉ በሙሉ ለጌታ ክፍት የሆነና ሙሉ በሙሉ በጌታ የተያዘ የያህዌ ተራራ፣ የጽዮን ተራራ አለ፤ በጽዮን የተመሰሉት ድል ነሺዎቹ ጌታ እንደ የክብር ንጉሥ መላውን ምድር እንደ መንግሥቱ የራሱ ለማድረግ ተመልሶ የሚመጣበት ምቹ የውጊያ ስፍራ ናቸው—መዝ. 24፡1-3፣ 7-10፤ ዳን. 2፡34-35፤ 7፡13-14፤ ኢዮኤል 3፡11፤ ራእ. 11፡15፤ 19፡13-14።

ቀ. ከመጸለይ ውጪ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ጫፍ፣ የክርስቶስ አካል እውነታ ጋር የሚደረስበት ሌላ መንገድ የለም፤ የክርስቶስ ሙሽራ ለመሆን እንደ የክርስቶስ አካል እውነታ ድል ነሺዎች መሆናችን ይህን ዘመን፣ የቤተ ክርስቲያንን ዘመን ይዘጋዋል፣ እንዲሁም በመንግሥቱ ዘመን ከድል ነሺዎቹ ጋር ይህችን ምድር ለመውሰድ፣ የራሱ ለማድረግ እና ለመግዛት ክርስቶስን እንደ የክብር ንጉሥ መልሶ ያመጣዋል—ቂ. 7-9፤ 20፡4-6፤ መዝ. 24፡7-10።

II. **የሳሙኤል የመጀመሪያው መጽሐፍ ከመንግሥቱ ጋር እንደ ንጉሥ (በዳዊት የተመሰለው) የክርስቶስን መምጣት በምሳሌ ያሳየናል፦**

ሀ. በኤሊ ሥር የነበረው አሮጌው የአሮናዊው ክህንነት ያረጀ እና የደበዘዘ ሆነ (1 ሳሙ. 2፡12-29)፣ እግዚአብሔር ለዘላለማዊው ኢኮኖሚው መፈጸም አዲስ ጅማሬ እንዲኖረው ፈለገ፦

1. የመሳፍንት መጽሐፍ ይዘት የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር መታመናቸውን፣ እግዚአብሔርን መተዋቸውን፣ በጠላቶቻቸው መሸነፋቸውን እና በአሳዛኝ ሁኔታቸው ወደ እግዚአብሔር በንስሐ መመለሳቸውን ይዟል፤ ወደ ጌታ ሲዞሩ፣ ከጨቋኞቻቸው እጅ የሚያድናቸው መስፍን አስነሳላቸው፣ ያ መስፍን ሲሞት ግን፣ ወደ ክፉ መንገዶቻቸው ተመለሱ፣ እንደገናም ተበላሹ (1፡1-2፤ 2፡11—3፡11)፤ ይህ በመጽሐፈ መሳፍንት ለሰባት ጊዜአት የተደጋገመ ዑደት ሆነ።

2. እስራኤል በመሣፍንት ሥር ሳሉች የነበራትን ታሪክ ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ዓመታት እየደገመችው ነበር፤ ነገር ግን ዛሬ እግዚአብሔር እውነተኛው ዳዊት የሆነውን ክርስቶስን እንደ ሚገዛው ንጉሥ ድል ነሺዎቹ "በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ" ከሚያበሩበት (ማቴ. 13፡43) ከአንድ ሺህ ዓመት መንግሥቱ ጋር የሚያመጡትን ሳሙኤሎችን፣ ድል ነሺ ናዝራዊያንን (ዘኁ. 6፡1-9 እና የግርጌ ማስታወሻዎች) ይፈልጋል።
3. በሰይጣናዊው ቀውስ መካከል ይህን ዘመን ከቤተ ክርስቲያን ዘመን ከአንድ ሺህ ዓመት መንግሥቱ ጋር ወደ ንጉሡ ዘመን ለሚቀይር ለሆነ አዲስ ነገር፣ ለአዲስ መነቃቃት ዛሬ ወደ ጌታ መመልከት ያስፈልገናል።

ለ. ለሳሙኤል መወለድ እግዚአብሔር ከሚታዩት ነገሮች በስተጀርባ ነገሮችን አነሳሳ፤ በአንድ በኩል፣ የሐናን ማኅፀን ዘጋ፤ በሌላ በኩል፣ "እግዚአብሔርም ማኅፀንዋን ዘግቶ ነበርና ... [ሐናን] ታስቆጣት ታበሳጫትም" ዘንድ ፍናናን አዘጋጀ (1፡5)፤ ሐና በየዓመቱም ወደ ያህዌ ቤት በምትወጣበት ጊዜ፣ ሐና እስከምታለቅስበት እና አንዳች እስከማትቀምስበት መጠን ድረስ ፍናና ታበሳጫት ነበር (ቁ. 6)።

ሐ. ይህም ጌታ ወንድ ልጅ ይሰጣት ዘንድ እንድትጸልይ ሐናን ገፋፋት፤ ለእግዚአብሔር ስእለት የተሳለችበት የሐና ጸሎት የተነሳሳው በሐና ሳይሆን በእግዚአብሔር ነበር፤ እግዚአብሔር በሐና ጸሎት እና በገባችው ቃል ተደሰተ፣ ማኅፀኗንም ከፈተ (ቁ. 10-11፣ 20)፤ ሐና ፀነሰች፣ ልጅ ወለደች፣ ሳሙኤል ብላም ጠራችው (ትርጓሜውም "በእግዚአብሔር ተሰማሁ" ወይም "ከእግዚአብሔር ጠየቅሁ" ማለት ነው)።

መ. እግዚአብሔር በሕይወት መስመር ከእርሱ ጋር አንድ የሆነችውን ሐናን ማነሳሳት ችሎ ነበር፤ የሕይወት መስመር እግዚአብሔር በምድር ላይ መንግሥቱ፣ እርሷም የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን (ማቴ. 16፡18-19፤ ሮሜ 14፡17-18፤ ኤፌ. 1፡22-23)፣ የሥስታንዱ አምላክ ሕይወታዊ አካል ትኖረው ዘንድ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ድሰታ ክርስቶስን የሚያመጣ መስመር ነው፤ እግዚአብሔር በሕይወት መስመር ከእርሱ ጋር አንድ የሆነ እንዲህ ያለ ሰው ማግኘት እስከቻለ ድረስ፣ በምድር ላይ መንገድ አለው (1 ሳሙ. 1፡1—2፡11፣ 18-21፣ 26)።

ሠ. በእርግጥ የሳሙኤል ምንጭ ሰው አልነበረም፤ ሉአላዊ እና ምሥጢራዊ በሆነ መልኩ ሕዝቡን ያነሳሳው እውነተኛው ምንጭ እግዚአብሔር ነበር፤ የሐና ጸሎት የእግዚአብሔር የልብ መሻት መስተጋባት፣ ንግግር ነበር፤ ያ ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ መከናወን ሰው ከመለኮታዊው እንቅስቃሴ ጋር መተባበር ነበር፦

1. የሐና ጸሎት የሚያመለክተው ለሐና ጸሎት በሰጠው መልስ የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ለእግዚአብሔር መሻት ፍጹም የሆነ ናዝራዊን፣ ድል ነሺን ለማፍራት እንደነበር ነው—1፡10-20።
2. ናዝራዊ ፍጹም በሆነ መልኩ ለእግዚአብሔር የተሰጠ፣ እግዚአብሔርን እንደ ንጉሡ፣ ጌታው፣ ራሱ እና ባሉ የሚወስድ እና ለዓለማዊ ደስታዎች ድሰታ ምንም አይነት ፍላጎት የሌለው ነው፤ ከመወለዱ በፊት እንኳን፣ ሳሙኤል እንዲህ ያለ ሰው ለመሆን በእናቱ የተሰጠ ነበር።

## III. የሳሙኤል የመጀመሪያው መጽሐፍ የሚያመለክተው ንጉሡን ከመንግሥቱ ጋር የሚያመጣውን አገልግሎት ነው፤ ይህን "የሐና አገልግሎት" ብለን ልንጠራው እንችላለን፦

ሀ. ፍናና እና ሐና መሠረታዊ በሆነ መልኩ ሁለት የተለያዩ መርሆችን እና መሠረታዊ በሆነ መልኩ ሁለት የተለያዩ አገልግሎቶችን ይወክላሉ (1 ሳሙ. 1፡2፣ 4፣ 7)፤ የሐና አገልግሎት ንጉሡን ለማምጣት ብቻ እንጂ ብዙ ልጆችን ለማግኘት አልነበረም፤ የፍናና አገልግሎት ብዙ ልጆችን፣ ማለትም፣ ብዙ ውጤት ያለው አገልግሎት ማግኘት ነበር፤ ፍናና እና ልጆቿ አብዛኛውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይወክላሉ፣ ነገር ግን አንዳቸውም ክርስቶስን እንደ የክብር ንጉሥ ከማምጣት ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም።

ለ. የሐና መንገድ ቀላል መንገድ አልነበረም፣ እንዲያውም በፍናና ማነጻጸሮች እና ማስቆጣቶች የበለጠ ከባድ ሆነ፤ ሐናዎች ለመሆን የሚፈልጉ ለስደት፣ ለመናቅ፣ ለማልቀስ እና ለመጾም ራሳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው።

ሐ. ይህ ምን ያህል ሰዎችን ማዳን የመቻላችን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር የድል ነሺ ቡድን የማግኘቱ ጉዳይ ነው፤ እግዚአብሔር መጸለይ እና መንግሥቱን ንጉሥ ከሆነው ክርስቶስ እና አብረውት-ከሚነግሡት ድል ነሺዎቹ ጋር ማምጣት የሚችሉ ሰዎችን ማግኘት ይፈልጋል።

መ. የሐና ጸሎት ለሳሙኤል መወለድ መንገድ ነበር፤ ጸሎቶቻችን የድል ነሺዎቹን መወለድ የሚያመጣ መሆን አለበት፤ ለድል ነሺዎቹ መፍራት በማየል ደረጃ በሰማያዊው አገልግሎቱ ከዐረገው ክርስቶስ ጋር አንድ በመሆን መጸለይ ያስፈልገናል—ራእ. 1፡4፤ 3፡1፤ 4፡5፤ 5፡6፤ 2፡7፣ 11፣ 17፣ 26-29፤ 3፡5-6፣ 12-13፣ 21-22።

ሠ. ሐና ያለ ወንድ ልጅ መቀጠል ወደ ማትችልበት ነጥብ መጣች፤ ወንድ ልጅ ማግኘት ወደሚገባት ነጥብ መጣች፤ በ1ኛ ሳሙኤል 1 ያለው ወንድ ልጅ ንጉሡን ከመንግሥቱ ጋር የሚያመጣውን፣ በራእይ 12 ያለውን ድል ነሺውን፣ ብዙዎች የተካተቱበትን ወንዱን-ልጅ በምሳሌ ያሳያል፦

1. የእግዚአብሔር ዋናው ዘመን-ቀያሪ እንቅስቃሴው እንደ ቀዳሚው ድል ነሺ ከክርስቶስ እና እንደ ተከታዮቹ ድል ነሺዎች ከእኛ በተዋቀረው በራእይ 12 ባለው ወንዱ-ልጅ ይታያል፤ እግዚአብሔር ይህን ዘመን ማጠናቀቅ እና ንጉሡን ከመንግሥቱ ጋር ማምጣት ስለሚፈልግ፣ ዘመን-ቀያሪ መሣሪያው የሆነውን ድል ነሺውን፣ ብዙዎች የተካተቱበትን ወንዱን ልጅ ይፈልጋል።
2. የወንዱ-ልጅ መነጠቅ ለቤተ ክርስቲያን ዘመን ፍጻሜን ያመጣል፣ የመንግሥቱን ዘመን ያመጣል፤ ከዚህ ንጥቀት በኋላ "አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ" የሚል ታላቅም ድምፅ በሰማይ አለ—ቁ. 10።

**IV. የሐና ልምምድ በምሬታችን መካከል ነፍሳችንን በጌታ ፊት ማፍሰስ እንደሚያስፈልገን ያሳያል (1 ሳሙ. 1፡6፣ 10፣ 15-16)፤ በዘጸአት 15 የእስራኤል ልጆች ወደ ማራ መራራ ውኃ መጡ፤ ሕዝቡ በሙሴ ላይ ሲያጉረመርሙ፣ "ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፤ እግዚአብሔርም እንጨትን አሳየው፥ በውኃውም ላይ ጣለው፥ ውኃውም ጣፈጠ"—ቁ. 22-25፡-**

ሀ. ጌታ ለሙሴ ያሳየው እንጨት የሕይወትን ዛፍ ያመለክታል፤ ራእይ 2፡7 ስለ "የሕይወት ዛፍ" ይናገራል፤ በግሪኩ እዚህ ጋር ያለው *እንጨት* የሚለው ቃል በ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡24 ጥቅም ላይ ከዋለው *እንጨት* ከሚለው ቃል ጋር አንድ አይነት ነው፡-

1. በራእይ 2፡7 ያለው የሕይወት ዛፍ የሚያመለክተው የተሰቀለውን (እንደ ቁራጭ እንጨት በዛፍ የተመለከተው) እና ከሞት የተነሣው (በእግዚአብሔር ሕይወት የተመለከተው—ዮሐ. 11፡25) ክርስቶስን ነው፤ ስለዚህ፣ ወደ መራራው ውኃ ውስጥ ሙሴ የጣለው እንጨት የተሰቀለው እና ከሞት የተነሣው ክርስቶስ እንደ የሕይወት ዛፍ ነበር ማለት እንችላለን።
2. በጸሎት ወደ ጌታ ስንጮኽ፣ እንደ ሕይወት ዛፍ የተሰቀለውን እና ከሞት የተነሣውን ክርስቶስ ራእይ ያሳየናል፤ በጸሎታችን በኩል ነፍሳችንን በጌታ ፊት በማፍሰስ፣ ይህን እንጨት ወደ ማንነታችን መራራ ውኃዎች ውስጥ እየጣልን ነው፤ ያኔ እነዚህ መራራ ውኃዎች ወደ መገኘቱ ጣፋጭ ውኃዎች ይለወጣሉ።

ለ. የሐና ጸሎት ከመራራ ሁኔታዎቿ እና ከመራራው ማንነቷ ወጣ (1 ሳሙ. 1፡6፣ 10)፤ እርሷም ለኤሊ "እኔስ ልብዋ ያዘነባት ሴት ነኝ፤...<u>በእግዚአብሔር ፊት ነፍሴን አፈሰስሁ፤</u> ኀዘኔና ጭንቀቴ ስለ በዛ እስከ አሁን ድረስ ተናግሬአለሁና" ብላ ነገረችው (ቁ. 15-16)፤ መዝ. 62፡8 "የሕዝብ ማኅበር ሁላችሁ፥ በእርሱ ታመኑ፥ <u>ልባችሁንም በፊቱ አፍስሱ፤</u> እግዚአብሔር ረዳታችን ነው" ይላል፤ እግዚአብሔርን ለመንካት የሆነው እንዲህ ያለው ጸሎት እውነተኛ በሆነ መልኩ ከልብ የተነገሩ ቃላትን ይዟል።

ሐ. በመራራ ሁኔታዎች ውስጥ በሆንን እና በማንነታችን መራራ በሆንን ጊዜ ሁሉ፣ ለጌታ እውነቱን በመንገር ነፍሳችንን ከልባችን ጋር ለጌታ ማፍሰስ ያስፈልገናል፤ እንዲህ ያለው ጸሎት ንጉሡን ከመንግሥቱ ጋር የሚያመጡትን ድል ነሺዎቹን ያፈራል።

መ. ወደ "መራራ ውኃዎች" ስንመጣ፣ ለውስጣዊ ፈውሳችን ብቻ ሳይሆን (ዘጸ. 15፡26) ይልቁንም ንጉሡን ከመንግሥቱ ጋር ለማምጣት—የአምላካችን ስም በምድር ሁሉ በሚልቅበት (መዝ. 8፡1)፣ እና የዓለም መንግሥት "ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ [በምትሆንበት]፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም [በሚነግሥበት]" (ራእ. 11፡15) ጊዜ—ከእርሱ ጋር የሚተባበሩ ድል ነሺ ናዝራዊያን ለመፍራታቸው እግዚአብሔር ሉአላዊ እና ምሥጢራዊ በሆነ መልኩ ሌላ ተስፋ በማሳጣት እንድንጸልይ እያነሳሳን እንደሆነ መገንዘብ አለብን።

*© 2021 Living Stream Ministry*